ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
FORUM FOR SOCIAL STUDIES (FSS)

CAFOD Just one world
SCIAF for a just world
Trócaire Working for a just world

ምርምር ስልማት

ካፎድ ስኪያፍ ትሮኬር(Calod Sciaf Trocaire) ወይም ሲ.ኤስ.ቲ አለም አቀፍ የልማት ድርጅት ሲሆን የሶስትዮሽ ጥምረትምነው:: የሴቶችን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ አቅም ለማጎልበት በተለያዩ ሀገራት እየሰራ ያለውይህ ጥምረት በአገራችን ስምንት ከሚሆኑና በተመሳሳይ ተግባራትላይከተሰማሩ ሀገር በቀል ድርጅቶች ጋር በመተባበር እየሰራ ይገኛል::ድርጅቱ ሴቶችን በኢኮኖሚና በማኅበራዊ አቅም ማሳደግ (Women Economic and Social Empowerment-WEE) የተሰኘ የአምስት ዓመት መርሀ ግብር ነድፎ እየተንቀሳቀሰ ያለ ሲሆን ስራውን ከጀመረም ሶስት ዓመታትን አስቆጥሯል:: ከዚህ በተጨማሪም ስራዎቹ በጥናትና ምርምር የታገዙ ይሆኑ ዘንድ ፎረም ፎር ሶሻልስተዲስ (ኤፍ ኤስ ኤስ)ከተሰኘ አገር በቀል የጥናትና ምርምር ተቋም ጋር በመተባበር እየሰራ ነው:: ጥናቶችን የማካሄዱ ዋና አላማም [illegible] አቅም ግንባታ ስራዎች ዙርያ የታዩትን አዎንታዊና አሉታዊ ለውጦችን እና ያጋጠሙ ችግሮችን በቅርበት በመከታተልና በማየት ውጤቶቹን [illegible] ለሚመለከታቸው አካላት በተለያዩ መንገዶች ማቅረብ ነው:: በጥናቶቹውስጥ የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ፣ [illegible] ውጤቶችን በአውደ-ጥናቶችና ሌሎች መድረኮች እንዲሁም በመገናኛ ብዙሀን ሲያሰራጩ ቆይተዋል:: በዚህ ጽሁፍ ሴቶች መብታቸውን [illegible] ተሳትፎ [illegible] እንቃኛለን::

መግቢያ

አገርን የመምራት ጥበብና የማስተዳደር ችሎታን ለማግኘት የሚገባንን ክህሎት ማዳበር አስፈላጊነት አያጠያይቅም::ከዚህ ባልተናነሰም ራስን አሳልፎ መስጠት እና ወኔያዊ ተግባራትን መፈፀምንም ይጠይቃል:: እንደሚታወቀዉ እስካሁን የአገር መሪነት ዙፋኑን በአብዛኛው ጊዜ የተቆናጠጡት ወንዶች ናቸው:: ሆኖም ግን ብዙም ያልተዘመረላቸዉሴቶች በአስተዳደር ዙርያ በተለያየ ጊዜያትና ቦታዎች ሚናቸው ከፍተኛ እንደነበረ የተለያዩ የታሪክ መዛግብት ይናገራሉ፡ያም ሆነ ይህበታሪክ የሴቶች ተሳትፎ፣ አስተወጽኦ እንዲሁም መብት እምብዛም ትኩረት ያጣ እንደሆነ ብዙዎች የሚስማሙበት ጉዳይ ነው:: ከዚህም ባለፈ የሴቶች በፖለቲካና አመራር ደረጃ ያሳዩት ተጋድሎ ከብዙሀኑ ታሪክ ጋር ተቀብሮ ቀርቷል ቢባል ማጋነን አይሆንም:: ለዚህም ደግሞ በአገሪቷ የሰፈነው የወንድ የበላይነት ዋነኛ ምክንያት ሲሆን አገሪቱ ያለችበት የድህነት ደረጃን ጨምሮ ፣ በጎ ያልሆነ የባህልና የልምድ ውስብስብነት እንደተጓዳኝ ምክንያት ይጠቀሳሉ:: እነዚህምተግዳሮቶችየሴቶችን የትግል ታሪክ ከመደበቃቸውም በላይ ሴቶችን ለመለወጥየሚደረጉ ጥረቶች ውጤታማ እንዳይሆኑ አሉታዊ አስተዋፅዖ ሲያደርጉ ቆይተዋል:: የሴቶች ያልተዳሰሱ የተሳታፊነት ውጤቶችን አጉልቶ ለማውጣት ከተፈለገ ደግሞ የሚመለከታቸዉ አካላት ርብርብ ያስፈልጋል:: እውነታው መሬት እንዲረግጥም ከተፈለገ እድል የተነፈጉትንና ግማሽ ያህል የህብረተሰብ ክፍሉን የሚይዙትን ሴቶች ማሳተፍና ያመጡትንም ለውጥ በየጊዜው መመዝገብ ጥቅሙ አያሌ ነው:: በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን ድፍን አስተሳሰብ ከመቀየር ባለፈ መልካም የሆኑ ተሞክሮዎችን ለሌሎች ለማካፈልም ይረዳል:: ይህን መሰረት በማድረግበዚህ ጽሁፍ የሴቶችንየፖለቲካ ተሳትፎታሪክ ወደኃላ ተመልሰን በጥቂቱ ለመዳሰስ እንሞክራለን:: ፅሁፉን ለማሰናዳት ከተለያዩ የአገራችን የታሪክ መዛግብት ያገኘናቸውን መረጃዎችን ከተለያዩ ጸሁፎች ጋር በማጠናከር በነበሩት ስርአቶች በመክፈል አቅርበናል::

ሴቶች በንጉሳዊ ስርአተ መንግስታት

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የነበረውን አድሏዊ ስርአት ተጋፍጠው መብታቸውን ያስከበሩ እና ሚናቸው ከማጀትና ከቤተሰብ አልፎ አደባባይ ወጥቶ ማንነታቸውና እርአያነታቸው ገዝፎ ፖለቲካን የቀየሩ አያሌ እንስት ነበሩ:: የታሪክ ባለሞያዎች እንደሚያስረዱት የሴቶች ንቅናቄ ከአገሪቱ መፈጠር ጀምሮ የተሳሰረ ነው:: ታሪክን የኋሊት ብንመለከት ከ20ኛው ክፍለ ዘመን በፊት በኢትዮጵያ ታሪክ የንጉሳዊያን ሚስቶችእናልጆችየሆኑሴቶች ፖለቲካን፣ሃይማኖትንናአስተዳደርንአዋህደውበአገሪቱታሪክው ስጥበተለያዩወቅቶችከፍተኛሚናተጫውተዋል:: አገራችን በዚህ መሰል አስተዳደር ስርዓት በምትመራበት ወቅት የንግስናውን ወንበር ከተቆናጠጡት ንጉሶች በስተጀርባ የነበሩት እንስቶች በትንሹም ቢሆን ትኩረት ያገኙና በመጠኑ የታወቁ ነበሩ:: ከነዚህም ታላላቅሴቶች ውስጥ የንጉስላሊበላሚስትመስቀል-ክብ ሯ፣የንጉስኢዛናናየኢዛናእናትንግስትሶፊያ፣የንጉስዘረያዕቆብሚ ስትንግስትእሌኒ፣የአጼልብነድንግልባለቤትሰብለወንጌል፣የግራኝ አህመድወይንምኢብንመሐመድባለቤትድልዋንባራ፣የንጉስልብነ ድንግልባለቤትእቴጌብርሃንሙግሳወይንምምንትዋብእንደዚሁም የአጼሚኒሊክባለቤትጣይቱብጡልይጠቀሳሉ::የታሪክጽሀፍቶች እንደሚተነትኑት ከሆነበተለይበ15ኛውክፍለ ዘመንበንጉስዘርአ ያዕቆብአመራርወቅትየሴቶችየፖለቲካሚናከፍያለበትወቅትእንደነ በረይገልጻሉ::ንጉስዘረያቆብሴትልጆቹንናሌሎችዘመዱየሆኑሴቶች ንቁልፍበሆኑየአስተዳደርቦታዎችበመሾምየሴትአስተዳደርእንዲስ ፍንፈርቀዳጅእርምጃንእንደወሰዱ ይነገራል::

እነዚህ በታሪካቸው ብዙ የሰሩ እንስቶች ብዙም ያልተነገረላቸው ቢሆኑም ያደረጉት ተጋድሎ ስማቸውን ሊያስጠራ እንደቻለ ይታወቃል። በእንጻራዊመልኩታሪካ፣ብተሻለ ሁኔታ የተጻፈላትንግስትእቴጌ ጣይቱነች:: እቴጌጣይቱበኢትዮጵያታ ሪክበወታደራዊተሳትፎከፍተኛውንሚናከተጫወቱትእንስቶች ውስጥበአብነትትጠቀሳለች::ጣይቱብልህ፣አስተዋይናጠንካራ ነቷ ለባሏአጼሚኒሊክበአጠቃላይአገዛዙዘመንየቅርብአማካሪበ መሆንአገልግላለች::ሚኒሊክለአገሩዘመናዊነትንከማስረጽአንጻ ርለውጭሃይሎችልበ-ቀናናእምነትያለውነበር::በተቃራኒውደግሞ ጣይቱ ተጠራጣሪነበረች::ይህአመለካከቷየሚኒሊክንየዋህነትናሁሉንተቀ ባይነትሚዛናዊእንዲሆንአድርጓል::

ሴቶች በአጼ ሃይለስላሴ ዘመነ መንግስት(1935-1967 ዓ.ም.)

የሃያኛውክፍለ ዘመን የመጀመሪያዎቹአመታትእምብዛምሳያ ልፍየፋሽስቱየጣሊያንመንግስትበአድዋየደረሰበትንውርደትለ መበቀልበጊዜውእጅግዘመናዊየሆኑየጦርመሳሪያዎችንናየሰለ ጠነየጦርሃይልንአደራጅቶበኢትዮጵያላይከፍተኛጥቃትንለመሰ ንዘርዳግም ተንቀሳቀሰ:: በአድዋ ጦርነት ያበረከቱትን ቁልፍ ሚና በጣሊያን ዳግም ወረራም ወቅት ኢትዮጵያውያንሴት፣ ልጅ፣ወጣትጎልማሳ፣አዛውንትሳይቀርበአገርፍቅርስሜትወ ራሪውንፋሽሽትጦርለመመከትተነሱ:: በዚህ ጊዜም የሴቶቹ ማህበራትም ሴቶችን በማደራጀት በጦርነቱ ለዘማችስንቅመሰ ነቅናፈትልልብስማዘጋጀት፣እህልበታጣምጊዜፍራፍሬበመልቀ ም፣ስራስርበማመስመብል ያሰናዱ ነበር::ከዚህ በተጨማሪም እንደ ቀደምት እናቶቻቸውከባሎቻቸው ጋርየዘመቱ ብዛት ያላቸው ሴቶች ነበሩ::ከነዚህም ውስጥ ከቡልጋ ወ/ሮ ልክየለሽ በያን ከመራቢቴ፣ ወ/ሮ አሰለፈች ክ/ስላሴ፣ ከወለጋ በኩል ወደ ሱዳን በወጣው ጦር ወ/ሮ ከበደች ስዩም እና ወ/ሮ ወርቅነሽ ሲሰያ ተጠቃሽ ናቸው:: ቁልፍ የሆኑ መረጃዎችን ለአርበኞች በማቀበል ስራም የተጠመዱና ኋላም ለተገኘው ነጻነት ቁልፍ አስተዋጽኦ ያበረከቱ ሴቶችም ነበሩ::ወ/ሮ ሸዋረገድ ገድሌ በአዲስአለምአካባቢይንቀሳቀስለነበረውአርበኛጠላትን ስልላመረጃ በማቀበልቁልፍሚናአበርክታለች::አርበኞችየአዲስአለምንየጠላት ምሽግለማጥቃትና ለማስለቀቅየቻሉትበቆፍጣናይቱወ/ሮሸዋረገድ ገድሌድጋፍጭምርመሆኑንየታሪክሰነዶችያመላክታሉ::

ኢትዮጵያ ከጣልያን ወረራ ነጻከወጣች በኋላ ቁጥራቸው አነስተኛ የሆኑ ሴቶች በመንግስት ስራዎችና በሌሎች አገልግሎቶች በሃላፊነት ተሰማርተው ለማገልገል በቅተው ነበር::ለሴቶች አመች ባልነበሩ ሁኔታዎች ውስጥ የሚኒስተርነትና የተለያዩ የመሪነት ድርሻን የተጫወቱ እንስቶች ነበሩ:: ከእነዚህ እንስቶች ውስጥ ወ/ሮ ስንዱገብሩ አንዷ ነበረች:: የሴት ልጅ መለኪያ ትዳር በመያዝና ቤተሰብ መመስረት በነበረበት በዚሁ ወቅት ወ/ሮ ስንዱ ያገኘቻውን እድል በመጠቀም የመጀመርያዋ የሴት የትምህርት ቤት ዳይሬክተር ለመሆን በቅታለች:: በዚሁ የስራ ዘርፍም ለ8 አመታትያህል አገልግላለች:: በጊዜዋምወላጆች ሴት ልጆቻቸውን እንዲያስተምሩ በማበረ ታታትሴቶችወደትምህርትቤትእንዲመጡከፍተኛአስተዋጽኦ አበርክታለች:: ከዚህ በተጨማሪም የኢትዮጵያ 2ኛው ህገ-መንግስት የሴቶች የመምረጥና የመመረጥ መብት ማፅደቁን ተከትሎ ወ/ሮስንዱገብሩየሴቶችየፖለቲካተሳትፎበፓርላማደረጃ በመወዳደር ሴቶች የፓርላማ አባል መሆን እንደሚችሉ ካሳዩት ሁለትእንስቶች መካከልአንዷምናት::በሌላ በኩልየታሪክ ዘገባዎች እንደሚያስረዱት በጣልያን ጦር ወረራ ምክንያት የተፈጠሩ አበይት ችግሮችን ለመቋቋም የሴቶች ቡድን ተመስርቶም ነበር:: ከእነዚህም ውስጥ አንዱን ለመጥቀስ ያህል በጦርነት ሳቢያ የተፈናቀለውን ህብረተሰብ ለማገልገል የተለያዩ ስልጠናዎች የሚሰጡበት የሴቶች አደረጃጀት ነበር::

ሴቶች በዘመነ ደርግ (1967-1983 ዓ.ም.)

በ1960ዎቹ የፊውዳሉን ስርአት ለመገርሰስ የተካሄደው የተማሪዎች ትግል በድል ተጠናቆ የነበረውን ስርዓት ሙሉ በሙሉ ለማጥፋት ቻለ:: በወጣቶች የተመራው ይህው ትግል ወጣት ሴቶችን በብዛት የተሳተፉበት እንደነበርም ይታወሳል:: የዚሁ ስርአት መውደቅም የደርግ መንግስት እንዲወለድ አድርጓል:: በዚህ ወቅት ታዲያ ለሴቶች መልካም ፍንጮችን ያሳዩ እድሎች አብረው መፈንጠቃቸው አልቀረም ነበር:: የተደነገገውም ህገመንግስት የሴቶች እኩልነትን በማኅበራዊ፣ በኢኮኖሚም ይሁን በፖለቲካዊ ጉዳዮች ዙርያ ሙሉበሙሉ የተቀበለ እንደነበር ይታወሳል:: የሴቶችንም መብት ለማስጠበቅ በሚል ርዕስ ሴቶችን በቡድን ማደራጀት [illegible] ነበር:: ከአምስት ሚሊዮን በላይ አባላትን ያቀፈው የአብዮታዊ ኢትዮጵያውያን ሴቶች ማህበር ወይም አ.ኢ.ሴ.ማ. ሴቶች እንዲደራጁ በማደረግ በአገርአቀፍ ደረጃ በስፋት ተመሰረተ:: ነገር ግን እነዚህማህበራት የሴቶችን መብት ከማስከበር ይልቅ ደርግ የሚከተለውን የፖለቲካ አላማ ለማስፈጸም የተተከሉ አደረጃጀቶች እንደነበሩ ይተቻሉ:: የሴቶችን መብት ራሳቸዉ ሲጥሱም ይስተዋሉ ነበር:: ህገ መንግስቱም ቢሆን ከወረቀት በዘለለ መልኩ ወደ ተግባር እንዳልገባና እውን እንዳልተደረገም ይነገራል::

በሌላ በኩል በደርግ ጊዜ በሴቶች ላይ ይደርስ የነበረውን ጭቆናን ለመታገል በተደረጉት ጥረቶች ውስጥም የሴቶች ሚና በርካታ እንደነበር ይነገራል:: "ያለሴቶች አብዮት ግቡን አይመታም" በሚል መፈክርም ከወንድ እኩል ተጋፍጠው የመብት ጥያቄዎችን ያነሱ እስከትግሉ ፍፃሜም ድረስ በትጋት የተጋደሉ ሴቶች አያሌ ነበሩ:: ለሴቶች በማይመች መልኩ የተሰሩትን እስርቤቶች የቀመሱና ብዙ ግፎችን ያዩም እንስቶችቁጥርም የሚናቅ አልነበረም:: አምባሳደር ታደለች ኃ/ሚካኤልም ከነዚህ እንስቶች ውስጥ አንዷ ስትሆን በእርግዝናዋ ወቅትም የተለያዩ ግፎችን ካየችና ለመብት የታገለችም ነበረች:: የደርግ መንግስትን በመቃወም የተመሰረቱትን የፖለቲካ ፓርቲዎች በመቀላቀልም በሰላማዊ ትግልም ተሳትፋለች:: ከዚህም ባለፈ የደርግ መንግስት ለመጣል የቻለው የኢትዮጵያ ህዝባዊ አብዮት ግንባር ነፃ አውጭ ድርጅት ውስጥ ከነበሩት ተቃዋሚዎች ውስጥ አንድ ሶስተኛ የሆኑት ሴቶች እንደነበሩም ታሪካዊ ፅሁፎች ይተነትናሉ::

የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ከ1983 - ዛሬ

ከደርግ ስርዓት በኃላ የመጣው የኢህአዴግ ስርዓት ለሴቶች መልካም የሆኑ ገጽታዎችን ከአለም አቀፍ ሁኔታዎች ጋር በተያያዘ ምልኩ አመጣ:: በአለምአቀፍ ደረጃየተከሰተው ጠቅላላ የሆነ የዴሞክራሲ ለውጥን ተከትሎ አገሪቷ በርካታ ለውጦችን እንድታስተናግድ አድርጓታል ይባላል:: የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እንቅስቃዎችም እየተስፋፉ መጡ:: የመደራጀት ነፃነትንም ተከትሎ የተለያዩ የሴቶች አደረጃጀቶች ተመሰረቱ::ከነዚህም ውስጥ አንዱና ዋንኛው የኢትዮጵ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር(ኢ.ሕ.ባ.ሴ.ማ.)የመጀመርያው የሴቶች አደረጃጀት በመሆን ተመሰረተ::በ1987ዓ/ም በወ/ሮ መአዛ አሸናፊ የተመሰረተው ይኸው ማህበር የሴቶችንመብትን ከማስጠበቅ አንፃር ከፍተኛ ሚናን እየተጫወተም ይገኛል:: ከዚህም ባለፈ የአዲስ አበባ ሴቶች ማህበር እና የኢትዮጵያ ሴቶች ማህበር ቅንጅትና የመሳሰሉት አደረጃጀቶች ተመስርተዋል::

በኢህአዲግ መንግስት የተለያዩ ፖሊሲዎች መውጣታቸው ለሴቶች ተሳትፎ መልካም መንገዶችን የከፈቱ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ ፖሊሲውን የሚያስፈፅሙ አካላት በውሳኔ ሰጭነት ደረጃ እንዲቀመጡ ተደርጎም ነበር:: የእነዚህ ውሳኔ ሰጭዎች የመሾም ዋና አላማም ልማትንና አንዳንድ ጉዳዮችን በሚመለከቱ የመንግስት እቅዶች ዙርያ ሴቶችን የሚወክሉ ጉዳዮች መግባታቸውን (mainstreaming) መከታተል ነበር:: በጊዜ ሂደት በፓርላማ ውስጥም ካሉ መቀመጫዎች ውስጥ 30% የሚሆኑት በሴቶች እንዲያዙም ተደርጓል:: በሴቶች የተቋቋሙት ቡድኖችም የሴቶች ፌዴሬሽን በሚል ስም በተመሰረተ ቡድን ውስጥ መካተት ጀመሩ:: ከጊዜ ሂደት በኋላ በብዙዎች እምነት የታጠለባቸው እኒሁ ለውጦችበሴቶች ኢኮኖሚው ማኅበራዊና ፖለቲካ ጉዳዮች ላይ የታሰበውን ግብ ሳያመጡቀርቷል:: በጊዜ ሂደት መልኩ የተቀየረውም ይኸው አሰራር የሴቶችን ሕይወት በመለወጥ ረገድ ተቀዛቀዘ::

በአጠቃላይ ሲታይ ግን በዘመነ ኢሕአዴግ ሴቶች በፖለቲካ ያላቸው ተሳትፎ የተሻለ እንደነበር በብዙሆን ይመሰክራል:: ለምሳሌ በ2009 ዓ.ም የታየው ጉልህ የሆነ ለውጥ እንደ አንድ ማሳያ ሊወሰድ ይችላል:: የሀገሪቱን ፕሬዘዳንት ጨምሮ ሌሎች ቁልፍ የተባሉ የሚኒስትር መስሪያ ቤቶች በሴቶች መመራታቸው የሚታወስ ነው:: ይህም ሴቶች በፖለቲካ እና ውሳኔ ሰጭነት ያላቸውን ተሳትፎ ከማሳደጉም በላይ በአገሪቷላይ የሰፈነውን "ሴት ልጅ አትችልም" የሚለውን አስተሳሰብ ፍጹም የተሳሳተ መሆኑን አሳይቷል:: በሌላ በኩል በአለማችን ላይ ትኩረት ካገኙ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሴታዊት እንቅስቃሴ (feminist movement) በአገራችን መጀመራቸው አንዱና ዋንኛው ነው:: ሴታዊት እንቅስቃሴ አንግቦ የተነሳውን ሴቶችን በኢኮኖሚ፣ ፖለቲካና ማህራዊ የመብት እኩልነት የማስጠበቅ ሁኔታ ከጀመረ የተወሰኑ አመታት ተቆጥረዋል:: ይህ በሴቶች በተዋቀረ ቡድን የተመሰረተው እንቅስቃሴ አጀማመር ሴቶች እርስ በርስ በሆነ ጉዳዮቻቸው ተረዳድተው ችግሮቻቸውን እንዲፈቱ የሚችሉበት መድረክን ለመፍጠር የታለመነበር:: ከጊዜ ሂደት በኋላ ግን መድረኮቹን ለሁሉም ክፍት በማድረግ ጠቅለል ባሉ ጉዳዮች ላይ በመወያየት የመፍትሄ ሀሳብን ማመንጨት የትኩረት አቅጣጫቸው አድርገው ቀይረዋል::ይህው እንቅስቃሴ ፖሊሲዎችና ህጎችሴቶችን ያማከሉና ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ለማድረግ ብዙ እየ[illegible] ነው:: ባደጉ ሀገራት የተጀመረው ይህው እንቅስቃሴ [illegible] ሀገራት ካስመዘገቡዋቸው ለውጦች ውስጥ በትምህርትና ስራ መስኮች ሴቶች ከወንዶች እኩል ተሳታፊነትና ተሰሚነትን እንዲያገኙ ማስቻል ይገኙበታል::